# እነ አቶ ስዬና የስምምነት ጥላቻቸው

## "አርባ ዓመት ውቅያኖስ ውስጥ የኖረ አለት መዋኘት አይለምድም"

**(ከልደቱ አያሌው)**

ቅዳሜ ህዳር 5 ቀን 2002 ዓ.ም ለህትመት በበቃው የአዲስ ነገር ጋዜጣ አቶ ስዬ አብርሃ ሰሞኑን 65 ፓርቲዎች፣ "የፓርቲዎች የሥነ-ምግባር ህግ" ረቂቅ ላይ ያደረጉትን ስምምነትና የተስማሙትን ፓርቲዎች በመቃወምና በማውገዝ (አንዳንድ ጊዜም በመሳደብ) የፃፉትን መጣጥፍ አነበብኩት፡፡ አቶ ስዬ ስምምነቱን እንደዚህ አምርረው የሚቃወሙት በሥነ ምግባር ደንቡ ላይ እኛ ያላየነው ምን ዓይነት ስህተት አግኝተውበት ይሆን? ብዬ በማሰብ መጣጥፉቸውን ያነበብኩት በጉጉት ነበር፡፡ ትንሽ እንዳነበብኩ የአቶ ስዬ ትኩረት በሥነ ምግባር ደንቡ ይዘት ላይ ሳይሆን በተስማሙት የፓርቲ መሪዎችና መሪዎቹ ስምምነቱን ሲያካሂዱ ስላደረጉት መጨባበጥ መሆኑን ሳይ ግራ ተጋባሁ፡፡ ጽሑፉ እየተገባደደ ሲመጣም አቶ ስዬ አብርሃ ይግረምህ ብለው የሥነ-ምግባር ሕጉ መሠረታዊ የይዘት ችግር እንደሌለበትና እንደማይቃወሙት በመግለፃቸው አቋማቸው ግራ ከማጋባትም አልፎ አስገረመኝ፡፡ በአንድ በኩል የሥነ-ምግባር ሕጉን ይዘት እየደገፉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ በሚደግፉት የሥነ-ምግባር ረቂቅ ሕግ ላይ የተደረገውን ስምምነት የሚያወግዙት አቶ ስዬ፣ በመጣጥፋቸው መቋጫ ላይ ደግሞ የአገሪቱ ፓርቲዎች ወደ ስምምነት እንዲመጡ እገዛ እያደረጉ የሚገኙትን ዲፕሎማቶች በማንቋሸሽና በማውገዝ ከማስገረምም አልፈው አስደነገጡኝ፡፡ መጣጥፉን አንብቤ ስጨርስም የአቶ ስዬ ጠብና ችግር በረቂቅ የሥነ-ምግባር ደንቡ ላይ ሳይሆን በዋናነት በ"ስምምነት" እና በ"ተስማሚዎች" ላይ መሆኑን ተገነዘብኩ፡፡ ስምምነትንና ተስማሚዎችን የመጥላት አባዜ (phobia) ደግሞ አስደንጋጭ ነው፡፡

አቶ ስዬ መጽሐፍ እየፃፉ እንደሆነ በቅርቡ ሰምቼ ታትሞ እስካነበው ቸኩዬ ነበር፡፡ የቸኮልኩበት ምክንያትም አቶ ስዬ ከህወሃት ከተለዩ በኂላ፤ ከኢትዮጵያ ጥቅም አንፃር ከህወሃት ጋር ያላቸው መሠረታዊ ልዩነት ምን እንደሆነ፣ ከ27 ዓመት በላይ የህወሃት አባል ሆነው ሲኖሩ ምን ዓይነት የሚያጸጽት ስህተት እንደፈፀሙ እና ከቀድሞ የትግል ጓደኞቻቸው ጋር ምን ዓይነት ሕዝብ ሊያውቀው የሚገባ ሚስጥር ተጋርተው እንደነበር አንድም ቀን ሲናገሩ ሰምቻቸው ስለማላውቅ ምናልባት ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ አገኝ ይሆናል ብዬ በማሰቤ ነበር፡፡ ይህንን በአዲስ ነገር ጋዜጣ የወጣ መጣጥፋቸውን ካነበብኩ በኂላ ግን አጉል ተስፈኛ መሆኔን ተረዳሁ፡፡

በሌሎች የታደሉ አገሮች እንደ አቶ ስዬ አብርሃ የአገር መከላከያ፣ እንደ አቶ ገብሩ አስራት የክልል ገዥ፣ እንደ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የአገር ርዕሰ ብሔር የነበሩ ታላላቅ ሰዎች ጡረታ ሲወጡ ለዜጎቻቸው የሚያስተምሩት ስለጥላቻ፣ ስለመራራቅና ስለ ጽንፈኝነት ሳይሆን ስለ መቻቻል፣ ስለመተባበርና በጋራ ጉዳዮች ላይ አብሮ ስለመስራትና አገርን ስለመገንባት ስለሆነ እኔም እነ አቶ ስዬን ከመሰሉ "ታላላቅ" ሰዎች የምጠብቀው ይንኑ ነበር፡፡ ነገር ግን እንደ አገርም ሆነ እንደ ትውልድ አልታደልንምና የምንመኘውን ማግኘት አልቻልንም፡፡ ዛሬ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ስለመደማመጥና የመቻቻል ፖለቲካ ብዙ ማወቅና መናገር በጀመሩበት ዘመን የ40 ዓመታት የፖለቲካ ልምድ አለን የሚሉና ዕድሜአቸው ለስልሣ ፈሪ የሆኑ አባቶቻችን በኩራት የሚያራምዱት "ፖለቲካ" ድርድርን መርገጥ፣ ስምምነትን ማንቋሸሽና ማውገዝ ሲሆን እየታየ ነው፡፡ ይህ የእነ

አቶ ስየ የወቅቱ “ፖለቲካ” አንድ አባባልን ያስታውሰኛል፡፡ ይኸውም፤ “አርባ ዓመት ውቅያኖስ ውስጥ የኖረ አለት ድንጋይ መዋኘት አይለምድም” የሚለውን፡፡ በርግጥም አርባ ዓመት በውሃ ውስጥ የኖረ አለት መዋኘት ይቅርና ጭራሽም አይረጥብም፡፡ አለትን ከአርባ ዓመት የውሃ ውስጥ ቆይታ በኋላ አውጥተን ብንጨምቀው ጠብታ ውሃ “ፍጭጭ” አይለውም፡፡ የነ አቶ ስዬ የአርባ ዓመት የፖለቲካ ልምድም እንደ አለቱ ለዴሞክራሲ ግንባታ የሚጠቅም “ፍጭጭ” የሚል ጠብታ የለውም፡፡

አቶ ስዬ! የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ተቀናቃኞቻችንን በሀሳብ የበላይነት ለማሸነፍ ሲያቅተን ቀላል ሆኖ የምናገኘው ስልት ተቀናቃኞቻችንን በልዩ ተልዕኮ አራማጅነት፣ በሰርጐ ገብነት ወይም በተለጣፊነት በመፈረጅ የፖለቲካ ስብዕናቸውን ለመግደል መሞከር ነው፡፡ እርስዎም በመጣጥፍዎ ላይ የተጠቀሙበት እንዲህ ዓይነቱን ከኢህአፓ ዘመን ጀምሮ ትውልድዎ ባህል አድርጐ ሲጠቀምበት የኖረውን ያረጀ ያፈጀ ስልት ነው፡፡ በእኔ በኩል ግን እርስዎን ለመሞገት የሚያስችል በቂ ሀሳብ አለኝ ብዬ ስለማምን የምሞግትዎ እርስዎ በመረጡት ዘዴና መንገድ ሳይሆን፤ ምክንያታዊ በሆነ የሀሳብ ክርክርና በተጨባጭ እውነታ (Facts) ላይ በመመስረት ይሆናል፡፡

## በስምምነቱ ሂደት ላይ ስላቀረቡት ትችቶች፤

አቶ ስዬ ረቂቅ የሥነ-ምግባር ሕጉን ምንም ዓይነት አቃቂር ሊያወጡለት ባለመቻላቸው እንደማይቃወሙት ገልፀዋል፡፡ አንድ ህሊና ያለው ሰው ስምምነት የተደረገበትን “ሠነድ” ደግፎ እያለ በሠነዱ ላይ የተደረገውን “ስምምነት” እንዴት መቃወም እንደሚቻል በራሱ እንቆቅልሽ ቢሆንም፣ አቶ ስዬም ሆኑ መድረክ ስምምነቱን እያወገዙ ይገኛሉ፡፡ አቶ ስዬ ስምምነቱን ለማጣጣል ቀደም ሲል መድረክ ሲደረድራቸው የነበሩ ሰበቦችን ሁሉ ወደ ጐን በመተው ሁለት ነጥቦችን በምክንያትነት ጠቅሰዋል፡፡ የመጀመሪያው “ኢህአዴግ መድረኩን ስለሚፈራው ከድርድሩ አገለለው” የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ “ኢህአዴግ በሌሎች አንገብጋቢ አጀንዳዎች ዙሪያ አልደራደርም በማለት ድርድሩን በሥነ-ምግባር ደንቡ ላይ ብቻ እንዲገደብ አደረገው” የሚል ነው፡፡ አቶ ስዬ ያቀረቧቸው እነዚህ መከራከሪያዎች የተዛቡ ብቻ ሳይሆን ነጭ ውሸቶች ናቸው፡፡ የመጀመሪያውን ምክንያት ብናይ፣ ድርድሩ ከተጀመረ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ መድረክን ለማግለል የተደረገ ምንም ዓይነት ሙከራ የለም፡፡ ወደፊትም መድረክ በፈለገው ጊዜ የድርድሩን ሂደት እንዲቀላቀል በሩ ክፍት ሆኖ እንዲጠብቀው ነው የተወሰነው፡፡ አቶ ስዬ ከፓርቲዎች ምክር ቤት መቋቋም ጋር በተያያዘም የምክር ቤቱ አባል ፓርቲዎች አራቱ ብቻ እንደሆኑና እነዚህ ፓርቲዎችም ከሌሎች ፓርቲዎች የተለየ ልዩ ጥቅም እንዳላቸው አድርገው የገለፁት ፍፁም ስህተት ነው፡፡ የምክር ቤቱ አባል ፓርቲዎች የሚሆኑት በአሁኑ ወቅት ሰነዱን የፈረሙት 65 ፓርቲዎች ሲሆኑ እነዚህ ፓርቲዎች የምክር ቤቱ አባል በመሆናቸውም ምንም ዓይነት የሚያገኙት የተለየ ጥቅም የለም፡፡ የተለየ ጥቅም ያገኛሉ የሚል ድንጋጌም በየትኛውም የስምምነቱ አንቀፆች ላይ አልሰፈረም፡፡

አቶ ስዬ “ኢህአዴግ በሌሎች አንገብጋቢ አጀንዳዎች ዙሪያ አልደራደርም በማለት ድርድሩን በሥነ-ምግባር ደንቡ ላይ ብቻ እንዲገደብ አደረገው” በማለት ያቀረቡት ትችትም ሐሰት ነው፡፡ የድርድሩ ሂደት ከተጀመረ ጀምሮ ኢህአዴግ ከቀድሞ ባህሪው በተለየ ሁኔታ በተቃዋሚዎች የቀረበና አልደራደርም ብሎ ገደብ የጣለበት ምንም ዓይነት አጀንዳ የለም፡፡ በዚህም ምክንያት ነው አራቱ ፓርቲዎች ባደረግነው ድርድር ከሥነ-ምግባር ደንቡ በተጨማሪ ወደፊት በሌሎች 16 አጀንዳዎች ላይ ለመደራደር

የተስማማነው፡፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ ኢህአፓን በመሰሉ ድርጅቶች ከሚቀርበው የሽግግር መንግሥት የማቋቋም ጥያቄ በስተቀር በእነዚህ 16 አጀንዳዎች ውስጥ ያልተካተተ አንድም ጥያቄ የለም፡፡ ለምሳሌ፤ አቶ ስዬ የመድረኩ ብቻ ጥያቄዎች ነበሩ በማለት ተቀባይነት እንዳላገኙ አድርገው ያቀረቧቸው ሁለት ጥያቄዎች ናቸው፡፡ የሚገርመው ግን እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ከ16ቱ አጀንዳዎች ውስጥ በግንባር ቀደምነት የተያዙ ናቸው፡፡

አቶ ስዬ ከገለጿቸው ከእነዚህ ሁለት ነጥቦች በተጨማሪም ቀደም ሲል በመድረኩ በኩል ሲደረደሩ የነበሩ ምክንያቶች በሙሉ አሳማኝ አልነበሩም፡፡ መድረኩ ከእነ ኢዴፓ ጋር አልደራደርም ማለቱ ከኢህአዴግ በባሰ ፀረ-ዴሞክራሲ አቋም የሚያራምድ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን፣ "የተለየ አጀንዳ ስላለኝ ከኢህአዴግ ጋር በተናጠል መደራደር አለብኝ" ማለቱም ሌሎች ፓርቲዎችን ከሂደቱ ለማግለልና እራሱን ያላግባብ አግዝፎ ለማሳየት የሚጠቀምበትን የሴረኝነት ስልት በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡ የመድረኩ አባል ድርጅቶች ከአንድ ዓመት በፊት በተለያዩ የሕግ ረቂቆች ላይ ከኢህአዴግ ጋር ቁጭ ብለው ሲደራደሩ እንዳልነበረ ዛሬ በድንገት "ፓርቲዎች በህግ ረቂቅ ላይ የመወያየት መብት የላቸውም" ማለታቸው፣ ከዚህም በተጨማሪ "ምርጫ ቦርድን ስለማናምነው ሊፈርስ ይገባዋል" እያሉ በተደጋጋሚ ክስ ማቅረባቸውን ረስተውት ዛሬ ደርሰው የምርጫ ቦርዱ መብት ተቆርቋሪና ምርጫ ቦርድን አማኝ በመሆን "ሰነዱን ምርጫ ቦርድ በባለቤትነት ከተረከበው እንወያይበታለን" ማለታቸው ምን ያህል በመርህ የማይገዙና ከድርድሩ ሂደት ምክንያት እየፈጠሩ መሸሽን የመረጡ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

## በተስማሙት ፓርቲዎች ላይ ስለቀረበው ትችት፤

የአቶ ስዬ ተቃውሞ እርሳቸው ጭምር ባልተቃወሙት የሥነ-ምግባር ረቂቅ ሕግ ላይ የተደረገውን ስምምነት ብቻ ሳይሆን በዋናነት ሰነዱን ተስማምተው በፈረሙት ፓርቲዎች ላይ ነው፡፡ በሰነዱ ላይ የፈረሙት 65 ፓርቲዎች ቢሆኑም፤ አቶ ስዬ ግን እነዚህን ፓርቲዎች እንደሌሉ በመቁጠር ማውገዝ የመረጡት አራቱን ፓርቲዎች ብቻ ነው፡፡ አቶ ስዬ ይህንን ያደረጉት ያለምክንያት አይደለም፡፡ የተደራዳሪ ፓርቲዎቹ ቁጥር ከአራት አልፎ 65 ሲደርስ መድረኩ የስምንት ፓርቲዎች ስብስብ ነው በማለት ቁጥር እየጠቀሱ "ታላቅነትን" ለማሳየት መሞከር አስቸጋሪ እየሆነ ስለመጣባቸው የስልሳ አምስቱን ፓርቲዎች መስማማት በፅሁፋቸው ውስጥ አንድም ቦታ ላይ ሳይጠቅሱት አልፈዋል፡፡ አቶ ስዬ እንደሚያስቡት የፓርቲዎች ቁጥር መብዛት ትልቅ ቁምነገር ከሆነ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ከአሁን ቀደም በኢዲኃህ (ህብረት) ስም 14፣ በደቡብ ኅብረት ስም 16፣ በኢተፖድህ ስም ከ20 በላይ፣ በአማራጭ ኃይሎች ስም 36 ፓርቲዎች አባል የሆኑባቸውን የተለያዩ ስብስቦች መርተው ውጤታማ ሳይሆኑ እንደቀሩ ቢገነዘቡት ይጠቅማቸው ነበር፡፡ አቶ ስዬ፤ "እኔ የመድረክ አባል ስለሆንኩ የተለየ ተዓምር ይፈጠራል" ብለው ካላሰቡ በስተቀር፣ በኢህአዴግ የውስጥ ትግል ተሸናፊ የሆኑ ጥቂት ሰዎች ከመጨመራቸው ውጭ በመድረክ ዙሪያ የተፈጠረ አዲስ ነገር የለም፡፡

የሆነ ሆኖ አቶ ስዬ በዋናነት አጉልተው ሊያሳዩትና ሊተቹት የፈለጉት ከስምምነቱም በላይ የአራቱ ፓርቲዎች ተወካዮች በስምምነቱ የፊርማ ሥነ ሥርዓት ላይ መጨባበጣቸውን በተመለከተ ነው፡፡ አቶ ስዬ በአንድ በኩል ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር የተደረገውን መጨባበጥ የከኃዲነትና የተለጣፊነት ድርጊት አድርገው ለማሳየት የሞከሩ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የእኔን (የልደቱን) እና የኢንጅነር ኃይሉን አለመጨባበጥ

ጥያቄ ሊነሳበት የሚገባ ጉዳይ አድርገው ሊያቀርቡት ሞክረዋል፡፡ አቶ ስዬ የሥነ ምግባር ደንቡን ጉድፍ አውጥተው ሊተቹት እስካልቻሉ ድረስ የፓርቲዎቹ መስማማትና መጨባበጥ ለምን ሊያበሳጫቸው እንደቻለ ለእኔ ግልፅ ባይሆንም፤ አቶ ስዬ ለ27 ዓመታት ተቃቅፈዋቸው ከኖሩት ከእነ አቶ መለስ ጋር የተቃዋሚ መሪዎች የአንድ ቀን መጨባበጥ ለምን ኃጢያት መስሎ እንደታያቸው የበለጠ ግራ ያጋባል፡፡ በአንድ የጋራ አገራዊ ጉዳይ ላይ ተቀዋሚ ፓርቲዎችና ገዥው ፓርቲ ሲስማሙና ሲፈራረሙ መታየቱስ የከኃዲነትና የተለጣፊነት ድርጊት ተደርጐ የሚታየው በምን ምክንያት ይሆን? እንዲህ ዓይነቱ ጭፍን ፍረጃ ስምምነትን ከመፍራትና ከመጥላት የሚመነጭ የግራ ፖለቲካ አስተሳሰብ ከመሆን አልፎ ሌላ አሳማኝ ምክንያት ሊቀርብበት የሚችል አይመስለኝም፡፡ ቀደም ሲል አቶ ገብሩ አስራት “ይህንን የሥነ ምግባር ደንብ የተፈራረሙትን ፓርቲዎች ከእንግዲህ ከኢህአዴግ ጋር አንድ ብሎክ (Block) አድርገን ነው የምናያቸው” በማለት እንደተናገሩት ሁሉ፤ አቶ ስዬም በመጣጥፋቸው ላይ ከኢህአዴግ ጋር የተፈራረሙትን ሦስት ፓርቲዎች አንድም ጊዜ “ተቃዋሚ ፓርቲዎች” አድርገው ሊጠሯቸው እንዳልፈለጉ በግልፅ አሳይተዋል፡፡

በእነ አቶ ስዬ እምነት አንድ ተቃዋሚ ፓርቲ ከገዥው ፓርቲ ጋር በአንድ ሰነድ ዙሪያ (ያውም ስህተት ባልተገኘበት) ተስማምቶ ስለተፈራረመ ብቻ ከገዥው ፓርቲ ጋር አንድ ብሎክ ተደርጐ የሚታይና “ተቃዋሚ ፓርቲ” የመባል መስፈርትን አያሟላም ከተባለ፤ ይህ አስተሳሰብ እነ አቶ ስዬ ያሉበትን መሠረታዊ የአስተሳሰብ ችግር በግልፅ ያሳያል፡፡ ምክንያቱም፣ በእንዲህ ዓይነቱ ስምምነት ውስጥ መግባት ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በኢህአዴግ ብሎክነት ወይም ተለጣፊነት ያስፈርጃል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ እነ አቶ ስዬም ሆኑ መድረኩ የሚያቀርቡትን ጥያቄ ኢህአዴግ የቱንም ያህል ቢቀበልም፤ በየትኛውም ዓይነት ሰነድና አጀንዳ ላይ ሊስማሙና ሊፈራረሙ አይችሉም ማለት ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው ለእነ አቶ ስዬ አብርሃ ተቃዋሚ ፓርቲ ማለት ከገዥው ፓርቲ ጋር በምንም ጉዳይ ላይ የማይስማማ፣ በጐም ሆነ መጥፎ ገዥው ፓርቲ የሚሰራውን ሁሉ በጭፍን የሚያወግዝና ከገዥ ፓርቲ አባላት ጋር ሲጨባበጥ መታየት የሌለበት ፓርቲ ነው ማለት ነው፡፡ እንግዲህ አርባ ዓመት ውቅያኖስ ውስጥ የኖረው አለትና የእነ አቶ ስዬ የአርባ ዓመት የፖለቲካ ልምድ “አንድና አንድ” የሚሆነው እዚህ ላይ ነው፡፡ እነ አቶ ስዬ ዕድሜ ልካቸውን በፖለቲካ ውስጥ ቢያሳልፉም ሠላማዊ ትግልም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እስካሁን ገና አልገባቸውም፡፡

ከዚህ አንፃር እነ አቶ ስዬ ሰላማዊ ትግልም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲ ምን ማለት እንደሆነ ገና ሊነገራቸው የሚገባ ቢሆንም፤ በእንዲህ ዓይነቱ የፖለቲካ “ሀሁ” ላይ ማብራሪያ መስጠት ለአብዛኛው የዚህ ጋዜጣ አንባቢ የማይመጥን በመሆኑ አልፈዋለሁ፡፡ ነገር ግን ለአቶ ስዬ ፖለቲካ ማለት መወያየትን፣ መደራደርንና መስማማትን መጥላት ከሆነ የጀመሩትን የጥላቻ ዘመቻ የሚያጠናክርላቸው ተጨማሪ መረጃ ልሰጣቸው እወዳለሁ፡፡ አቶ ስዬ! የፊርማው ሥነ ሥርዓት በተፈረመበት እለት እኮ እኔና ኢንጅነር ኃይሉ ከመጨባበጥም አልፈን ለሩብ ሰዓት ያህል ጐን ለጐን ቆመን በጐ ሀሳብ ተለዋውጠናል፡፡ አቶ ስዬ! ባይገርምዎ የፊርማ ሥነ ሥርዓቱ ከተከናዎነ ከአራት ቀናት በኋላ አቶ በረከት፣ ኢንጂነር ኃይሉ፣ አቶ አየለና እኔ ከሌሎች አባሎቻችን ጋር ሆነን በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን እራት ስንበላ አመሸን እኮ! አቶ ስዬ! ባይገርምዎ በቀደም እለት ከኢህአዴግ ባለሥልጣናት ጋር በአንድ መኪና አብረን ተጉዘን የተከዜን ግድብ መርቀን ተመለስን እኮ! አቶ ስዬ! ይህንን መረጃ የምሰጥዎት ለእርስዎ የኢህአዴግ ብሎክ ወይም ተለጣፊ መሆን ማረጋገጫው እንዲህ ዓይነቱን ተግባር መፈፀም ከሆነ ድካምዎ

እንዲቃለል በማሰብ ነው፡፡ አቶ ስዬ ዘነጉት መሰለኝ እንጂ በዚያው መጣጥፍዎ ላይ ጓደኛዎ አቶ ገብሩ አስራት ኢንጅነር ኃይሉ በሚመሩት የተቃዋሚዎች ስብሰባ ላይ በመስቀል አደባባይ ተገኝተው ንግግር በማድረጋቸው ምክንያት ብዙ ውግዘት የደረሰባቸው መሆኑን በመቃወም ጽፈዋል፡፡ ታዲያ ይህ ዓይነቱ አቶ ገብሩ ላይ ሲሆን ትክክል የሚሆነው መርህዎ እኛ ላይ ሲሆን ስህተት የሚሆነው ለምን ይሆን? አቶ ስዬ የመርህ ሰው ቢሆኑ ኖሮ በአንድ መጣጥፍ ላይ እንደዚህ ሃሣብዎ እርስ በርሱ ባልተቃረነ ነበር፡፡

## ያለፈ ታሪካችንን በተመለከተ ስለተሰጠው አስተያየት፤

አቶ ስዬ በአንድ በኩል የእኛን ደካማነት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የመድረክን ጠንካራነት ለማሳየት ሲሉ ያለፈ ታሪካችንን ለመዳሰስ ሞክረዋል፡፡ “በመስታወት ቤት ያለ ሰው ቀድሞ ድንጋይ አይወረውርም” ይባላል፡፡ አቶ ስዬ ግን መጣጥፋቸውን ሲሞነጫጭሩ ይህንን እውነታ ረስተውታል፡፡ አቶ ስዬ እኔ ልዩ ተልዕኮ ያለኝ ሰው መሆኔን ለማሳየት የተጠቀሙበት አንዱ ስልት ሌሎቹ የቅንጅት አመራሮች ሲታሰሩ እኔ ሳልታሰር መቅረቴን ነው፡፡ ይህንን የአቶ ስዬን ትችት በጥያቄ መልክ ለመመለስ ልሞክር፡፡ አቶ ስዬ እርስዎ እንደሚሉት ሃቀኝነት የሚለካው በመታሰርና አለመታሰር ከሆነ እኔ እንደ በግ አምስት ጊዜ ታስሬ ስፈታ የዛሬዎቹ የትግል ጓደኞችዎ እነ ፕሮፌሰር በየነና ዶ/ር መረራ እስከ ዛሬ ድረስ የእስር ቤትን ደጅ ሳያዩ የኖሩት የኢህአዴግ ተለጣፊዎች ስለሆኑ ነው? በአሁኑ ወቅት ወ/ሪት ብርቱካን ስትታሰር የዘመኑ ወዳጆችዎ እነ ኢንጂነር ግዛቸው እንደገና ሳይታሰሩ የቀሩት የኢህአዴግ ተለጣፊዎች ስለሆኑ ነው? እሩቅ ሳንሄድ ከህወሃት ክፍፍል በኋላ እርስዎ ታስረው ሲማቀቁ የትግል ጓደኞችዎ የሆኑት እነ አቶ ገብሩ አስራት ሳይታሰሩ የቀሩት የወያኔ ተለጣፊ ስለሆኑ ነው? አቶ ስዬ! የቀድሞ የትግል ጓደኞችዎ ሰዎችን የማሰርና ያለማሰር መመዘኛቸውንና የቆረጣ ስልታቸውን ከእኔ የተሻለ እርስዎ ያውቁታልና ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ቢሰጡ መልካም ነው፡፡ ለነገሩ አቶ ስዬ አልሰሙ ይሆናል እንጂ “ልደቱ እኮ የወያኔ ተልዕኮ አራማጅ ነው” የተባለው ገና እርስዎ “የወያኔ” ባለሥልጣን ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ስለሆነ ዙሪያ ጥምጥም ከመዞር ለምን ባለሥልጣን በነበሩበት ጊዜ ስለእኔ (ስለ ልደቱ) ወያኔነት የሚያውቁትን መረጃ አይነግሩንም?

ሌላው አቶ ስዬ በእኔ ላይ ያቀረቡት ክስ የፖለቲካ አክሮባት የምችል ሰው መሆኔን በመጥቀስ ነው፡፡ አቶ ስዬ እኔ አርባ ዓመት ሙሉ ውቅያኖስ ውስጥ የኖረው አሳ አይነት እንዳልሆንኩ ቢያውቁ ኖሮ ይህንን ለመናገር ባልደፈሩ ነበር፡፡ አቶ ስዬ አርባ ዓመት ሙሉ አንድ ዓይነት የፖለቲካ አቋምን ኃይማኖት አድርጐ መያዝ ሞያ መስሎ ስለሚታያቸው የፖለቲካ አክሮባት ሲያዩ ቢደነግጡ አያስደንቅም፡፡ በርግጥም አቶ ስዬ የፖለቲካ አክሮባት ቢያውቁ ኖሮ በህወሃት ክፍፍል ጊዜ የፖለቲካ አክሮባት አዋቂ በሆኑት በእነ አቶ መለስ ክፉኛ ባልተሸነፉ ነበር፡፡ አቶ ስዬ! ለእኔ ፖለቲካ ማለት የመሆን ጥበብ ነው (Politics is the art of possible) ፖለቲካ ራስን ከወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር እያጣጣሙ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም አቋምን እያስተካከሉና እየለወጡ ወደፊት መራመድ መቻልን የሚጠይቅ ራሱን የቻለ ሳይንስ ነው፡፡ ስለሆነም እኔ የምመክርዎ አርባ ዓመት ሙሉ አንድ ቦታ ላይ ተቸክሎና ገርሮ የቀረውን የፖለቲካ አቋምዎን ትንሽ የሚያፍታታ የፖለቲካ ጅምናስቲክ እንደኔ እንዲለማመዱ ነው፡፡

አቶ ስዬ እኔን በአክሮባት ሰሪነት የከሰሱኝ ከቅንጅት በመለየቴ ነው፡፡ በርግጥም ቅንጅት በተሳሳተ አቋም ላይ እንደነበረና በፖለቲካ አክሮባት አስፈላጊነት በማመን ራሴን ከቅንጅት አውጥቻለሁ፡፡ በቅርቡ በመድረክ ውስጥ አብረውዎት ሲሰሩ የነበሩትን የዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያምን የይቅርታ ጥያቄ ቢያነቡት ስለ እኔ አክሮባት ትክክለኛነት በቂ መልስ የሚያገኙ ይመስለኛል፡፡ አቶ ስዬ የፖለቲካ አክሮባት ባለማወቅዎና በኢትዮጵያ ጉዳይ ሳይሆን "ህወሃት በያዘው አመለካከትና አሰራር እንዳለ መቀጠል አለበት እንጂ መታደስ የለበትም" በማለት በድርጅትዎ ውስጥ የተጀመረውን የተሃድሶ እንቅስቃሴ ተቃዋሚ ሆነው በመቆምዎ የደረሰብዎትን ሽንፈት አይተውታል? በርግጥም የእርስዎ "ያለመታደስ" አቋም አሸናፊ ሆኖ ቢሆን ኖሮ ዛሬ በአገራችን ተቃዋሚና ነፃ ፕሬስ ኖሬው እኔና እርስዎ እንደዚህ ለመከራከርም ባልበቃን ነበር፡፡ ትናንት ህወሃት ውስጥ ሆነው ተሃድሶን ከተቃወሙ፣ ዛሬ ደግሞ ተቃዋሚ ሆነው ከሌሎች ጋር መወያየትንና ቁጭ ብሎ መደራደርን ሲያወግዙ ከታዩ፣ የህወሃትን የውስጥ ትግል አሸንፈው ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ቢሆን ኖሮ፤ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓትና የመናገር ነፃነት በዚች አገር ሽታቸው እንደማይኖር ሰሞኑን እያራመዱት የሚገኘው ስምምነትን የመጥላት አቋምዎ በግልፅ ያሳያል፡፡ ከወቅቱ አቋምዎ የምንረዳው ቁምነገር፣ እርስዎ በህወሃት የውስጥ ትግል እንዴት ተሸናፊ ለመሆን እንደበቁ ብቻ ሳይሆን ከአገር ጥቅምም አንፃር መሸነፍዎ ትክክልና የሚገባ መሆኑን ጭምር ነው፡፡

"ጅብ የማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል" እንደሚባለው አቶ ስዬ በአሁኑ ወቅት ለአገር ጉዳይ ተቆርቋሪና የተቃዋሚው ጉራ "ፊት አውራሪ" ሆነው ለመታየት ሲሞክሩ እያየን ነው፡፡ ግን እስኪ በስሜትና በጉራ ሳይሆን በተጨባጭ እውነታ ስለአለፈ ታሪካችን እንነጋገር ከተባለ፣ አቶ ስዬ የኤርትራን የቅኝ ግዛት ጥያቄ እውቅና ከመስጠት ጀምሮ እስከ ቅርቡ የባድመ ጦርነትና የህወሃት የውስጥ ክፍፍል ድረስ ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም ሲሉ ይዘውት ስለነበረ አንድ አቋምዎ እስኪ ሊነግሩን ይድፈሩ? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ መድፈር የማይችሉ ቢሆንም ቢያንስ ግን ከዛሬ ባላንጣዎችዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በአገርና በሕዝብ ጥቅም ላይ አብረው ሲዶልቱ መኖርዎንና ተቃዋሚዎችና ሕዝቡ ለመብታቸው መከበር ሲያደርጉት የነበረውን ትግል ሲያፍኑ መኖርዎን ባይዘነጉት መልካም ነው፡፡ "ጦርነትን መዋጋት ብቻ ሳይሆን መስራት እንችላለን" እያሉ በትእቢት ከመገሸር በስተቀር እንኳንስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለትግራይም ሕዝብ የፈየዱት ቁምነገር የለም፡፡ የእርስዎ የትግል ውጤት፣ የትግራይ ሕዝብ በጨለማ ውስጥ ተውጦ እያለ ለራስዎ ዘመዶች ጀነሬተር ከመትከል ያለፈ ትርጉም እንዳልነበረው የአደባባይ ሚስጥር መሆኑን ባይዘነጉት መልካም ነው፡፡

አቶ ስዬ መርዛማ ስልታቸውን በመጠቀም እኔ (ልደቱ) የትግራይን ሕዝብ ልዩ ተጠቃሚ አድርጌ እወነጅል እንደነበርም ጽፈዋል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አባባል ግለሰቡ ምን ያህል ከሴረኝነትና ከዘረኝነት ፖለቲካ እንዳልራቁ የሚያሳይ ቢሆንም፤ እኔ ግን የምታወቀውና ከዛሬ 10 ዓመት ጀምሮ የቮካል ዲያስፖራው የአሉባልታ ዘመቻ ሰለባ እንድሆን ያደረገኝ አቋም "ጥቂት በሥልጣን ላይ የተቀመጡ ሰዎች እንጂ የትግራይ ሕዝብ ከሌላው ሕዝብ የተለየ ተጠቃሚ አይደለም፡፡ በእኔ ዕምነት እንኳንስ የትግራይን ሕዝብና የኢህአዴግን መሪዎችም ጭምር እንደ ጠላት አላያቸውም" ብዬ መናገሬ ነበር፡፡ በርግጥ አቶ ስዬ የጠሉብኝ እርሳቸው ሲመሯቸው የነበሩትን የፓርቲ የንግድ ድርጅቶች መቃወሜን ከሆነ ዛሬም አምርሬ የምቃወም መሆኔን ሊገነዘቡት ይገባል፡፡

በአጠቃላይ፤ አቶ ስዬ የእኛን ያለፈ ታሪክ ለመገምገም ባደረጉት ግምገማ አንድ ማጠቃለያ ላይ መድረሳቸውን በአንድ ምሳሌ ገልፀውልናል። ይኸውም፤ በፈረንሳይ አብዮት ወቅት ናፖሊዮን ቦናፓርት እና ሉዊ ናፖሊዮን የተባሉ ሁለት ስማቸው ተመሣሣይ የሆነ መሪዎች እንደነበሩና እነዚህ መሪዎች በፈረንሳይ ታሪክ የነበራቸው ስፍራ ግን የተለያየ እንደነበር ነግረውናል። ይህ የአቶ ስዬ ምሳሌ የቀረበው በአሁኑ ወቅት ስምምነት የተፈራረምነው ፓርቲዎች ከቀድሞው ቅንጅት የተለየን መሆኑን ለማሳየት ነው። በርግጥም የቀድሞው ቅንጅትና እኛ በብዙ ርቀት የተለያየን ነንና ምሳሌያቸው ከእኛ አንፃር ስህተት የለውም። ነገር ግን ይህንን የአቶ ስዬ ምሳሌ ከራሳቸው ማንነት ጋር በማነፃፀር ልናየው ብንሞክር፣ ከሁለቱ ናፖሊዮኖች የተለያዩ ከመሆን በተቃራኒ በትጥቅ ትግሉ ወቅት የነበሩትና በአሁኑ መድረክ ውስጥ የሚገኙት ሁለቱ "ስዬዎች" ግን ምንም ዓይነት ልዩነት የሌላቸው የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው። ግን እኮ አቶ ስዬ፣ ይህችን የቦናፓርቲዝም ትንታኔ ዛሬ ሳይሆን ከህወሃት የውስጥ ትግል በፊት አጥንተዋት ቢሆን ኖሮ ምንአልባት በአቶ መለስ የቦናፓርቲዝም ትንታኔ ከመሸነፍ ልታድንዎ ትችል ነበር።

## የኃይል አሰላለፍን አስመልክቶ ስለተሰጠው ትንታኔ፤

አቶ ስዬ ስለወቅቱ የፓርቲዎች የኃይል አሰላለፍ ትንታኔ ሲሰጡ ስለመድረክ ጠንካራነትና አዲስ ተስፋነት የሰጡት የመጀመሪያው ማብራሪያ መድረኩ የስምንት ፓርቲዎች ጥምረት መሆኑን በመጥቀስ ቢሆንም፤ ስምንት ፓርቲ መሆን በራሱ እንዴት የጥንካሬ መለኪያ ሊሆን እንደሚችልና ከቀድሞዎቹ የፕሮፌሰር በየነ "ኅብረቶች" በምን እንደሚለይ አላብራሩም። ስለመድረኩ ጥንካሬ በሁለተኛነት ያቀረቡት ምክንያት ደግሞ በመድረኩ ውስጥ ያሉ መሪዎችን ስም በመዘርዘር ሲሆን የእነዚህ ሰዎችን ስም መዘርዘሩ ወይም ሰዎቹ ፕሮፌሰሮችና ዶክተሮች መሆናቸው ከመድረክ ጥንካሬ ጋር እንዴት እንደሚያያዝም የጠቀሱት ነገር የለም። በሦስተኛነት የጠቀሱት ምክንያት በመድረኩ ውስጥ የሚገኘውና በ97 ምርጫ የተወዳደረው ኅብረቱ ወደ ፓርላማ የገባ መሆኑንና እንደ ቅንጅት ያልተከፋፈለ መሆኑን ነው። አቶ ስዬ በአንድ በኩል የኢዴፓን ፓርላማ መግባት የፖለቲካ አክብሮት በማለት እየከሰሱ በሌላ በኩል ፓርላማ መግባትን የኅብረቱ ጠንካራነት መገለጫ አድርገው ማቅረባቸው ያው መርህ የለሽ መሆናቸውን የሚያሳይ ቢሆንም፤ ከሁሉም በላይ የሚገርመው ግን የቅንጅት መከፋፈል ወለል ብሎ የታያቸው አቶ ስዬ፣ ከአሁኑ መድረክ በእጥፍ 14 ፓርቲዎችን አቅፎ የነበረው ኅብረቱ ብትንትኑ ወጥቶ በአሁኑ ወቅት በውስጡ ሁለት ፓርቲዎችን ብቻ ይዞ መቅረቱ ፈፅሞ ሊታያቸው አለመቻሉ ነው። አቶ ስዬ እነዚህን በመሰሉ ውሃ የማይቋጥሩ መከራከሪያዎች መድረክን ጠንካራ ድርጅት አድርገው ለማቅረብ ቢሞክሩም የአንድ ድርጅት ዋና መለኪያ ስለሆነው የድርጅታዊ መዋቅር ጥንካሬና የፖለቲካ አጀንዳ ጉዳይ ግን አስተያየት ሊሰጡ አልደፈሩም።

አቶ ስዬ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የሚገደዱበት ወቅት ከፊታችን እየመጣ መሆኑንም የተገነዘቡት አይመስልም። አቶ ስዬ እንደዚህ የሚመኩበት መድረክ የምርጫ ዘመቻ ሲጀመር ለፖሊሲ ክርክር እሳቸውን ወክሎ ቢልካቸው የርሳቸውን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አጀንዳ፣ ወይንስ የፕ/ር በየነን የሶሻል ዴሞክራሲ አጀንዳ፣ ወይንስ የኢንጅነር ግዛቸውን የሊበራል ዴሞክራሲ አጀንዳ ይዘው እንደሚከራከሩ ቀድመው ቢያስቡበትና የሚያስከትለውን ውጤት ለመገመት ቢሞክሩ ዛሬ ስለ መድረኩ ታላቅነት ለማውራት ባልደፈሩ ነበር። በምርጫ ክርክር ወቅት የመድረክ መለስተኛ ፕሮግራም ያላካተታቸው

ጥያቄዎች ከሕዝብም ሆነ ከመገናኛ ብዙሃን ሲቀርቡ “ይህንን ለጊዜው እናልፈዋለን” ወይንም “መንግሥት ከሆን በኋላ እንመልሰዋለን” ማለት የማያዋጣ ጨዋታ መሆኑን አቶ ስዬ ቢያጤኑትትና ከወዲሁ መፍትሔ ቢያፈላልጉ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ በዚህ ረገድ መድረኩ ያለበትን መሠረታዊ ችግር አቶ ስዬ እንደ ወታደር ሳይሆን እንደ ፖለቲከኛ በአግባቡ ማሰብ ከቻሉ፣ ያሰቡበት ቦታ የማያደርሳቸውን ፈረስ እየጋለቡ መሆኑን ሳይውሉ ሳያድሩ መገንዘብ የሚያቅታቸው አይመስለኝም፡፡ በርግጥ አቶ ስዬ የቀድሞ የትግል አጋሮቻቸውንና የዛሬ የፖለቲካ ባላንጦቻቸውን በተገኘው መንገድ ሁሉ ማዋከብ ከሁሉም በላይ የሚበልጥባቸው በመሆኑ እንጂ፣ መድረክ በተፈጥሮው የትም የማያደርስ ፈረስ መሆኑን ትንሽ ትንሽ አልጠረጠሩም ማለት አይቻልም፡፡ አቶ ስዬ “አልጠረጠርኩም” ካሉ ሌላ ማንም ሳይሆን ራሱ መድረክ ሊጠይቃቸው የሚገባን አንድ አስቸጋሪ ጥያቄ እዚህ ላይ መልሰው ማለፍ አለባቸው፡፡ ይኸውም፤ እውነት አቶ ስዬ መድረክ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚበጅ አጀንዳ ያለው ድርጅት ነው ብለው ካመኑ ለምንድነው እርስዎ ከመድረኩ ስምንት አባል ድርጅቶች በአንዱ ውስጥ አባል ሆነው መታቀፍና መስራትን ያልፈለጉት? አቶ ስዬ! የእርስዎን ፖለቲካ ቀረብ ብሎ ለሚያሽት ሰው የያዙት ትግል የድሮ የትግል ጓደኞችዎን ከመበቀል ያለፈ የአገር ጉዳይ መሆኑን አጠራጣሪ የሚያደርገው እንዲህ ዓይነቱ መርህ የለሽ አካሄድዎ መሆኑን ቢገነዘቡት መልካም ነው እላለሁ፡፡